*የሚያዚያ 9 ቀን 2010 ዓም*

# *ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ*

ጀግና ፋኖዎች የየዕለት ዉሎቸውን በድል እያሸበረቁ የመጣባቸውን እያጋደሙ ማንነታችንን እያስመሰከሩ ናቸው፤ ሰማዕት የሆኑ እነጎቤ እነ የመቶ አለቃ ደርቤ አደራ ብለው ያለፉት መራራ መስዋዕት አጋም ሆኖ እበኢተኛ ወያኔዎችን እየነደፉቸው ነው፤ የክፉ ቀን ዉሎአቸው የዉሻ ሞት እንዲጎነጩ እያደርጋቸው ነው፤ ወያኔዎች የተለያዩ ስሞችን በመፍጠር ራሳቸውን ቢያታልሉም ፋኖን ሊቋቋሙ እንደማይችሉ ከጅምሩ እየታየ ነው፤

*ከላይ በጠቀስነው ቀን ወያኔዎች ሰበብ ፈልገው ሰሜናዊ ጎንደር ዳባት ወደ አንድ ሥርግ ቦታ መኖሩ መረጃ ይሰማሉ፥ የወያኔ ታጣቂዎች ለሥርጉ ሲሉ ፋኖዎች ይመጣሉ የሚል መረጃ ስለሰሙ በዚያ አጋጣሚ በቦታው የሚገኙ ታዳሚዎችን ትጥቅ ለማስፈታት ያቅዳሉ፣ ታሪክ ሠሪዎቹ ፋኖዎች ተጋጅተው ከቦታ ተገኙ፥ ጎኑን ያልተጠራጠረ የወያኔ ታጣቂዎ ጎምለል! ጎምለል! እያለኡ ከድግሱ ቤት በራፍ ሲደርሱ ቆፍጣኖቹ ፋኖዎች ዓልመው ታጣቂ ባባይ እና ታጣቂ አራርሳ በተባሉት ላይ አንዳንድ አረር ሲያሳርፉ የተቀሩት መታኮሻ ቦታ ይዘው ፈልገሽ ምቺ ብለው ጥይት ማንጣጣት ሲጀምሩ ፋኖዎቹ ሌሎችንም አቁስለው ድግሱን ላለመረበሽ ሲሉ በሰላም ወደ ቀጠናቸው ሲመለሱ ሐፍረት የማይሰማቸው የወያኔ ታጣቂዎች ታዳሚውን እያንገላቱ እያንገላቱ ናቸው፣*

*የወያኔ ታጣቂዎች ሁለቱ አስከረናቸውን አቅፈው ወደ ኮማንድ ፖስታቸው ቢመለሱም ሕዝቡ እንዲጠቁማቸው አሁንም እያሰቃዩዋቸው ናቸው፣ በዳባት ጉድ የሠሩ ከዚህ ቀደም ሦስት የወያኔ ታጣቂዎችን ከማይመለሱበት እንደሸኙዋቸው መዝገባችን ይመሰክራል፣ የጀግኖቹን ስምና አድራሻ የማናወጣው ለድህንነታቸው ሲባል ነው፣ በርግጥ የፋኖዎችን ዝርዝር ገድል የማናወጣው ለደህንነታቸውና ለበተሰቦቻቸው ሰላም ሲባል ነው፣ በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳሰብ የምንፈልገው...ጉልቻ....ቢለወጥ....ወጥ....አያጣፍጥም፣ የሚለው ቃል ፋኖ ያምናል፣ የፋኖ የመጀመሪያ ግብ ...በኢትዮጵያ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ መምጣት አለበት ነው....በጥገናዊ ለውጥ የሚሽረግድ ካለ ለወያኔ ዕድሜ መራዘም ለኢትዮጵያውያን ሰቆቃ መስፋት የሚመኝ ብቻ ነው፣*

*አንድነታችን ለዘለዓለም ተከብሮ ይኖራል!!*

*ፀረወያኔ ትግላችን ግቡን ይመታል!!*

EPNP.INFO

ኢ.ሕ.ብ.ፓ

EPNP

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY